# <u>አስቸኳይ ጥሪ ለሚመለከታቸው ሁሉ</u>

## ከኢሮብ መብት ተማጓች ማህበር/ኢ.መ.ተ.ማ.

ነሓሴ 2002 ዓ.ም. ***የኢሮብ ወጣቶችን ከቀያቸው የማፍለስ ንግድ ባስቸኳይ ይቁም*** በሚል ርእስ፤ ጉዳዩ ያሳሰባቸው የብሄረሰቡ ተወላጆች አንድ መግለጫ አውጥተው በተለያዩ የኢትዮጵያውያን ድረ-ገጾች ማሰራጨታቸው የሚታወስ ነው። ቀጥሎም የኢሮብ ማብሎ (www.irobmablo.org) ድረ-ገጽ ይፋ እንደሆነ ***የኢሮብ አናሳ ብሄረሰብ ህልውና ላይ ተጽእኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ መሰረታዊ ችግሮችና መንስኤዎቻቸው*** በሚል ርእስ አቶ በየነ ገብራይ በጻፉት መጣጥፍ ውስጥም ለወጣቶቻችን ስደት ምክንያት ናቸው ያሉዋቸውን ችግሮች በዝርዝር አመላክተው እንደነበረ የሚታወስ ነው ። ከዚህም በተጨማሪ፤ አቶ ሱመ ***ለኢሮብ ወጣቶች ስደት ሶስቱ ዓበይት ምክንያቶች*** በሚል ርእስ ሥር በጻፉት መጣጥፍ ውስጥ ለኢሮብ ወጣቶች ስደት ምክንያት ናቸው ያሏቸውን ምክንያቶች በሶስት ርእስ ለይተው በዝርዝር ያሰፈሩትን አንብበናል።

የተለየዩ ጸሃፊዎች በተለያየ ጊዜ የወጣቶቹን አስከፊ የስደት ጉዞና የሚያጋጥሙ ችግሮችን አስመልክቶ ብጽፉና የሚመለከተው አካል መፍትሔ እንዲያፈላልግ ቢማፀኑም፣ ወላጆቻቸውም ሁኔታውን ለመለወጥ የተቻላቸውን ሁሉ ቢሞክሩም፣ በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ያለው ቤተዘመድ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ምክሩን ቢለግስም በአከባቢያቸው የሚታይ ተስፋ ለማየት ያልታደሉት ወጣቶች የሚሰጣቸውን ምክር ለማዳመጥ የሚያስችል ሁኔታ ሊፈጠርላቸው አልቻለም። ስለሆነም የሚሰጠውን ባዶ ምክር ለብቻው ሕይወት ሊሰጣቸው ባለመቻሉ አሁንም ለስደት እንዲዳረጉ አስገድዷቸዋል። ዛሬም እንደ ትናንቱ በሲናይ/ግብጽና በየመን በረሃዎች በሚገኙ ድብቅ ካምፖች በርካታ ወጣቶች ታጉረው እንደሚገኙ ኢ.መ.ተ.ማ ከውስጥ አዋቂ ምንጮች ባገኘው መረጃ ለማረጋገጥ ችሏል። እነዚህ የሚሰደዱ ወጣቶች መከፈል ያለበት ገንዘብ ካልከፈሉ ከነዚህ የማጎሪያ ካምፖች በህይወት የመውጣት ዕድላቸው የመነመነ እንደሆነም በግልጽ የሚታወቅ ነው። በሲናይ ሆነ በየመን በረሃ እነዚህ የማጎሪያ ካምፖች የመሰረቱ ማፊያዎች ከያንዳንዱ ሰው የሚጠይቁት ክፊያ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ እንደሚሄድና አሁን ከ6000 እስከ 10,000 ዶላር እንደደረሰ ገንዘቡን ከፍለው ወደ እስራኤል ወይም ወደ ሳዑዲ ዓረቢያ ከተሻገሩ ወጣቶች ባገኘነው መረጃ ለማረጋገጥ ችለናል።

በሲናይ/ግብጽ ሆነ በየመን በረሃዎች ታጉረው ያሉ ወጣቶች ሁኔታ ካለይ እንደተጠቀሰው ሆኖ እያለ ሌሎች እስከዛሬ ድረስ በትክልል የደረሱበት ያልታወቀ በመቶዎች የሚቆጠሩ ወጣቶች መኖራቸውም ኢ.መ.ተ.ማ  ሁኔታውን በቅርበት ከሚከታተሉ ወገኖች ለማወቅ ችሏል። ከነዚህ አድራሻቸው ካልታወቁ ወጣቶች የተወሰኑት የሞት አደጋ ገጥሟቸው እንዳይሆንም ስጋት መኖሩ እየተነገረ ነው ። የተቀሩት ደግሞ የሚጠብቃቸውን መዘዝ ምን ሊሆን እንደሚችል በውል ሳይገነዘቡ ወደ ሲናይና የመን ማጎሪያ ካምፖች በማምራት ላይ ሊሆኑ እንደሚችሉ፤ ወይም የተጣለባቸውን የገንዘብ መጠን መክፈል አቅቷቸው ባልታወቁ ማጎሪያዎች ውስጥ በመሰቃየት ላይ ሊሆኑ እንደሚችሉ ግምት ውስጥ ሊገባ የሚገባው እውነታ ነው

ኢ.መ.ተ.ማ. እነዚህ ወጣቶችን ከቤታቸው ጀምሮ እስከ ሲናይና የመን ድረስ መስመር በመዘርጋት በዜጎች ሕይወት በመነገድ ላይ የሚገኙ ወንጀለኞች፣ ከራሱ ከኢሮብ ብሄረሰብ፣ ከትግርኛ ተናጋሪው ኤርትራውያንና ትግራያውያን፣ ሱዳናውያን፣ ግብጻውያንና የመናውያን የተውጣጡ በሰው ሕይወት የሚነግዱ ቡድኖች እንዳሉ ሁኔታውን በቅርበት ከሚከታተሉ ምንጮች ለማረጋገጥ ችሏል። ኢ.መ.ተ.ማ እነዚህን ወጣቶች ለዚህ አስከፊ ስደት እየመለመሉ ለዓረብ ነብሰበላዎች ከሚያስረክቡት ውስጥ ከኢሮብ ብሄረሰብ የተወለዱ ወገኖቻችንን እንደሚጨምር በሚጠቅሱ መረጃዎች እጅጉን እንደሚያዝንና ጊዜው ሲፈቅድ ህዝቡ በሕግ ሊፋረዳቸውም እንደሚገፋ ለመግለጽ ይወዳል። ስለሆነም ለነዚህ በወጣቶቹ ችግርና ሞት ለመክበር ለተነሱ ስግብግብ ነብሰበላዎች ይህ እኩይ ተግባራቸውን ባስቸኳይ እንዲያቆሙ ይጠይቀል፣ ለሚመለካታቸው ሁሉም የሚከተለውን ጥሪ ያስተላልፋል።

1. ለትግራይ ክልላዊ መንግስት፣ ለወጣቶቹ ስደት ምክንያት የሆኑትን እንቅፋቶች ሁሉ ለማስወገድ ልዩ ቱክረት በመስጠት፣

    ሀ) .እነዚህ ለባዕድ ነብሰበላዎች የገዛ ወገኖቻቸውን በገንዘብ እየሸጡ ያሉትን ዘጎች በቁጥጥር ሥር በማዋል አስፈላጊውን ሕጋዊ ቅጣት በመቅጣት ከዚህ የወንጀል ተግባር እንዲቆጠቡ እንዲያደርግ፤
    ለ) ለነዚህ ወጣቶች መሰደድ ምክንያት የሆኑትን ችግሮች ከራሱ ከወጣቱና ከብሄረሰቡ አባላት ጋር በመምከር አስፈላጊ መፍትሄ እንዲያፈላልግለት፤

2. በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር ለሚገኙ የኢሮብ ብሄረሰብ አባላት በሞላ፣

    ሀ). ወጣቱ ትውልድ ወደዚህ አደገኛ ሁኔታ ራሱን እንዳያስገባ በተገኘ አጋጣሚ ሁሉ መተላለፍ ያለበትን መልእክት እንዲያስተላልፉ/ድታስተላልፉ፣
    ለ) ይህ የጋራ ችግራችን ስለሆነ በምንችለው ሁሉ የኢትዮጵያ መንግስት ባለስልጣናትን አጠቃላይ በተለይ ደግሞ ለትግራይ ክልል መንግስት ይህ የወጣቶች ስደት ይቆም ዘንድ መወሰድ ያለባቸው አስፈላጊ እርምጃዎችን ሁሉ እንዲወስዱ እንድንጠይቅ፣
    ሐ.) ሶስተኛ ዓቅም በፈቀደ ሁለ በተናጠልም ሆነ በቡድን ለሰብአዊ መብት ተሟጓች ድርጅቶችና፣ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ልዩ ልዩ አከባቢያዊና ዓለም አቀፋዊ ድርጅቶችና መንግስታት ጉዳዩን እንዲያውቁትና አስፈላጊ እርምጃ እንዲወስዱ እንድንናሳስብ ኢ.መ.ተ.ማ ጥሪውን ያቀርባል።

የወጣቶቻችን ችግር በጋራ ለመፍታት በአንድነት እንረባረብ!!!

ኢ.መ.ተ.ማ

መጋቢት 1 ቀን 2003 ዓ.ም.ኢ.